# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


## የታሰሩ መሪዎችን ለማስፈታት በጋራ እንንቀሳቀስ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲመሩት በፍላጎቱ የመረጣቸውና አመኔታውን የጣለባቸው መሪዎች ለሕገ-ወጥ እስር ከተዳረጉ እነሆ አሥረኛ ወራቸውን ይዘዋል:: ማንም ሕዝብ ወድዶና አምኖ የመረጣቸው መሪዎቹን አሳስሮ ስለሰላምና ስለዴሞክራሲ ማሰብ አይችልም:: እነኝህ መሪዎች የሚገኙት በጤናቸው ላይ ዘለቄታዊ እክል ወይም በሕይዎታቸው ላይ አደጋን የሚጋብዝ ሁኔታ ውስጥ ነው:: የአገዛዙም እቅድ እነሱን በእስር ላይ በማቆየትና የእስር ጊዜአቸውን ሰበብ አስባቡ በማጓተት ቀስ በቀስ እንዲረሱና ዘንቦ ተባርቆ ቆይተው ቢፈቱም እንኳ ያሉበት ሁኔታ በሚያስከትልባቸው ልዩ ልዩ የጤና እክል ምክንያት ትግሉን ለመቀጠል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ከሚል ስሌት የተቃኘ ይመስላል:: ኢትዮጵያውያን እነኝህ መሪዎች አሁን ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ መፍቀድ አይኖርብንም:: ስለሆነም መሪዎችን ለማስፈታት ኢትዮጵያውያን በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተቀናበረ እንቅስቃሴ አለማድረግ የኢሕአዴግ አምባ-ገነኖች እንደሚመኙት እነኝህን የኅሊናና የፖለቲካ እስረኛ መሪዎች ከመርሳትና አገዛዙ በይዞታው እንዲቀጥል ከመፍቀድ ውጭ ሆኖ ሊታይ አይችልም:: አሁን በተያዘው ሁኔታ በግልፅ የሚታይና ኅብረተሰባችንን በጋራ የሚያሰልፍ እንቅስቃሴ ከሌለና "ዝምታው" ከቀጠለ የአንዳንዶቹን በሕይዎት ያለመኖር የምንሰማበት ጊዜ እሩቅ ላይሆን ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለን:: ታዲያ ያኔ መቆጨቱና መጮሁ አግባብ ይሆናል?

ውድ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ አስተዋዩ፥ ታጋሹና ለዝንት-ዓለም እንግልት የተዳረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልዩነት አንድነትን፥ ከገዥዎች በጉልበት ላይ የተመሠረተ የሥልጣን ዝውውር አዙሪት ይልቅ በራሱ ይሁንታና ፈቃድ በመረጣቸው መሪዎች የመተዳደርን፥ ከእኔ አውቅልሃለሁ የአምባ-ገነኖች የጭቆና ሥርዓት ይልቅ ዴሞክራሲን በመምረጥ ነበር ግንቦት ሰባት ቀን ፺፯ ዓ/ም ዓለም ያደነቀውና ወገንን ሁሉ ያኮራ ሕዝበ-ውሳኔ የሰጠውና ታሪክ የሠራው:: ይሁንናም ከራሳቸው ጠባብ ዓላማ ሌላ የማይታያቸው አርቆ ማየት የተሳናቸው የሥልጣን፥ የግል ጥቅምና የሕዝብ ደም ጥመኛ የሆኑ ጥቂት የኢሕአዴግ አምባ-ገነኖች የሥርዓት ለውጥ የወለደውን ሂደት ለመቀልበስ በማሰብ ድምፁን በነፈጋቸው ሕዝብ ላይ ወገን ይሠራዋል ተብሎ የማይጠበቅ በቀል የወለደው አረመኔአዊ የሽብር ዘመቻ ከፍተው እነሆ ላለፉት አሥራ-አራት ወራት ቁም ስቅሉን እያሳዩት ነው::
በውስጥም በውጭም ያለው ኢትዮጵያዊ በተለይም ወጣቱ ክፍል ከየካቲት ፷፮ ወዲህ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በአገር መውደድና በወገን ፍቅር ስሜት የመልካም ሥርዓት ጥሙን ለማርካት አኩሪ እንቅስቃሴ አድርጓል:: አለኝታነቱን አስመስክሯል::
በሰኔ አንድ ፺፯ የንፁህ ዜጎችን ደምና የወላጆችን እንባ በማፍሰስ የተጀመረው የኢሕአዴግ አምባ-ገነኖች በሕዝባችን ላይ የታወጀ የሽብር ዘመቻ ሕዝብ አመኔታውን የጣለባቸውን መሪዎች፥ የነፃው ፕረስ አሳታሚዎችና ጋዜኞችን፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት መሪዎችን፥ የግብረ-ሰናይ ተቋማት ሃላፊዎችን፥ ወዘተ... በግፍ እስር ማሰቃየቱን ቀጥሏል::

የኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን ገዥዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝባችን በተለይም በወጣቱና በተማሪው ላይ የዘረጉትን የአፈና መረብ እንዳጠናቀቁና ሕዝቡን 'ሰጥ ለጥ አድርገናል፥ ተቃውሞ በርዷል' በሚል ትምክህት ይኽንኑ የሕዝብ ተቃውሞን የማፈን ከይሲ ሥራቸውን በኋላ-ቀር ከፋፋይና አረመኔአዊ አገዛዛቸው ላይ የተነሳሳውና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን እውን እንዲሆን አኩሪ የጋራ እንቃቃሴ በማድረግ ላይ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ባለው ከአገሩ ውጭ በሚኖረው ኢትዮጵያዊ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እረጅም የጥፋት እጃቸውን ለመዘርጋት አጥብቀው በስሊት እየተንቀሳቀሱ ይገኛል። እረዳት መንግሥታትንና ገንዘብ ለጋሽ ተቋማትን አገር ሰላም እንደሆነና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሰፈነ ለማግባባት በከፍተኛ ወጭ የውጭ ጉዳዬ-ፈጅ (ሎቢይስት) ከመቅጠር ጀምሮ ከሰባ-ሰባት ሚሊዮን ሕዝብ መብትና ጥቅም ይልቅ የራሳቸው የሥራ ዋስትና የበለጠባቸውና ለአምባ-ገነን አገዛዙ በዕድሜ-ቀጥልነት አገልጋይ ሆነው የተሰለፉ የሌቦች ዋሻ የሆነው የኢሕአዴግ ሕገ-ወጥ ፓርላማ አባል የሆኑ ጥቂት ራስ-ወዳድ ግለሰቦችን በማስማራት፥ በአንዳንድ ጥቅማ-ጥቅምና በልዩ ልዩ መንገዶች ኅብረተሰቡን ለመከፋፈልና ተቃውሞን ለማዳከም ሲባዝኑ ይታያል።
ይኸ መቸም ከአንድ ለኀልውናው የሞት የሽረት ትግል ከሚያደርግ ተስፋው የሰለለ ክፍል የሚጠበቅና እንግዳ ያልሆነ ነገር ነው። እንግዳ ሆኖ መታየት ያለበትና ኅብረቱን እያሳሰበ ያለው ግን የተቃዋሚው እንቅስቃሴ የሕዝባችንን መስዋዕትነት የማይመጥን፥ ፍላጎቱን የማያሟላና ጥያቄውን የማይመልስ እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ ነው።

ለአገራችን ውስብስብ ችግሮች በእርቅና ሰላም ላይ የተመሰረተ መፍትኄ እንደሚያስፈልግ የታመነ ነው። እርቅና ሰላም እንዲኖር ደግሞ በተፃራሪው ወገን የተሰለፉ ክፍሎች ፍላጎቱ፥ ቁርጠኝነቱና ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል። ምናልባት በአካሄዱ ላይ ካልሆነ በስተቀር በተቃዋሚው ክፍል የዚህ ችግር የለም ማለት ይቻላል። ችግሩ ያለው አሁንም በኢሕአዴግ በኩል እንደሆነ ግልጽ ነው። ኢሕአዴግ ደግሞ ይኸንን ለአገራችንና ለሕዝባችን ዘለቄታዊና አስተማማኝ ምላሽ ሰጭ እርምጃ አዎንታዊ መልስ ሊሰጥ የሚችለው ሲገደድ ብቻ ነው። ኢሕአዴግን አስገድዶ ወደ ድርድር ለማምጣት  የመጀመሪያው ሥራ ተቃዋሚው የጠራ መሠረት ላይ የተጣለ ትብብርና ግልፅ አጀንዳ እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ከአሁን በፊት ደጋግመን እንዳልነው ሁሉ በግልፅ አጀንዳ መንቀሳቀስና የሕዝቡ ትግል የጠራ መሥመር እንዲይዝ ማድረግ በአገራችን ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ ከሚታገልና ሃላፊነት ከሚሰማው የተቃዋሚ ክፍል ሁሉ ይጠበቃል። በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ የውጭ ኃይሎች ተወካዮችና ከተቃዋሚው ክፍልም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ከአኢሕአዴግ ጋር ድርድር እንዲደረግና ለቀጣዩ ምርጫ ዝግጅት እንዲደረግ ሽር ጉድ ሲባል በትዝብት እያየን ነው።
ኢዴኃኅ (ኅብረት) እንደዚህ ዓይነቱን አካሄድ ኢሕአዴግ የጀመረውን የሕዝብ ድሎች ቅልበሳ የሚያግዝና ሕዝባችንን ለቀጣይ አምባ-ገነን አገዛዝ ሥርዓት አጋልጦ የሚሰጥ አደገኛ አዝማሚያ አድርጎ ያየዋል። ከሁሉ አስቀድሞ ከኢሕአዴግ ጋር ስለ ወደፊቱ የአገራችን ዕድል ድርድር ከመታሰቡ በፊት ሕዝቡ የመረጣቸው ወኪሎቹና መሪዎቹ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታና በአስቸኳይ መፈታት ይኖርባቸዋል። የተቃዋሚው ክፍል ከኢሕአዴግ ጋር ትርጉም ያለው ድርድር ማድረግ የሚችለው እነኝህ መሪዎች የድርድሩ አካል ሲሆኑና ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ እንዳቀረብነው ሁሉ ማንኛውም ድርድር ሕዝቡ በግልጽ ያወቀውና የተሳተፈበት ሲሆን ብቻ ነው። ስለሆነም የታሰሩ መሪዎችና የነፃው ፕረስ አባላት መፈታት ከአሕአዴግ ጋር ለሚታሰብ ድርድር ሁሉ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። እነኝህን የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች ለማስፈታት ኢዴኃኅ (ኅብረት) በተቃዋሚ ለተሰለፉ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ልዩ ልዩ ስብስቦች እንዲሁም ለወገን ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚከተለውን ጥሪ ያቀርባል።

መሪዎቹን የማስፈታት ሃላፊነት የማንም የግል ጉዳይ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ እንደመሆኑ በዚህ ዙሪያ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ተባብረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ከጥር ፰ እስከ ፳ ቀን ፲፳ ዓ/ም የተካሄደው የኅብረቱ ሁለተኛ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እስረኞቻችንን ለማስፈታት የሚደረገውን ጥረት አስተባብረን እንድንረባረብና ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ለመቋቋም እንድንችል አንድ “የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል” በጋራ እንዲቋቋም ጥር ፲፰ ቀን ፲፳ ዓ/ም ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ደብዳቤ መፃፋችንና በጋራ እንድንሠራ መጠየቃችን በዚሁ ቀና መንፈስና የሃላፊነት ስሜት ነበር። በኦነግ

በተጠራው የሆላንዱ ስብሰባም ላይ ይኸንኑ የፖለቲካና የኅሊና እስረኞቻችን ጉዳይ ማንሳታችን በዚሁ መንፈስ ነበር፡፡ አሁን ስላለፈው ጊዜ ጊዜ ሳናጠፋ የፖለቲካና የኅሊና እስረኞቻችንን በማስፈታቱ ረገድ አዲስና ልዩ ትኩረት በአስቸኳይ እንዲሰጥ ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) የሚከተለውን አሳብ በቀና መንፈስ ያቀርባል፡፡

1. "ዜጎች ለታሰሩ መሪዎች" በሚል ስያሜ አንድ ሁሉን-አቀፍ የጋራ ግብረ-ኃይል በአስቸኳይ ማቋቋም፤
የዚህ ግብረ-ኃይል ተግባር የታሰሩ መሪዎችን፥ የነፃውን ፕረስ ባልደረቦችና ሌሎች የፖለቲካና የኅሊና እስረኞችን ለማስፈታት ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ መንገድና እረድፍ የሚያደርጉትን ዓለም-አቀፍ እንቅስቃሴ በሃላፊነት ማቀናበርና ማስተባበር ይሆናል፡፡ ይኸ ግብረ-ኃይል በአንድ የሲቪክ ወይም የሙያ ማኅበር ወይም ታዋቂ ግለሰብ ሃላፊነት የሚመራና ከሐይማኖት ተቋማት ሦስት ተወካዮች፥ ከታሰሩት ቤተሰቦች ሁለት ተወካዮች፥ ከሕግ ባለሙያዎች ሦስት ተወካዮች፥ ከኢሰመጉ አንድ ተወካይ፥ ከወጣቶች አንድ ተወካይ፥ ከሴቶች አንድ ተወካይ፥ ከኪነት አንድ ተወካይ፥ ከፖለቲካ ድርጅቶች (ከኅብረት፥ ከቅንጅትና ከኦነግ አንዳንድ) ሦስት ተወካዮች በአባልነት ይኖሩታል፡፡ ይኸ ግብረ-ኃይል የታሰሩ መሪዎችን ለማስፈታት ኢትዮጵያውያን የተባበረ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉና በሕግ በኩልም መወሰድ የሚችሉትን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል፡፡ ግብረ-ኃይሉ ሥራውን በቅልጥፍና ለመሥራት እንዲችል ከመሃሉ አራት አባላትን መርጦ ከአስተባባሪው ጋር በድምሩ አምስት አባላት ያሉት ሥራ አቀናባሪ አካል ቢኖረውና ተግባሩን በሁለት ንዑስ ክፍሎች ማለትም በሕግ ረገድ በሚሠራው ላይ የሚያተኩር 'የሕግ ክፍል'ና ሕዝብን የሚቀሰቅስና አደራጅቶ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ተግባራዊ የሚያደርግ አንድ 'አንቀሳቃሽ ክፍል' ቢኖሩት የተሻለ ይሆናል፡፡

2. ግብረ-ኃይሉ አስረኞቹን ለማስፈታት በዓለም ዙሪያ የሚሠሩ የኅብረቱን፥ የቅንጅቱና የሌሎች ድርጅቶችን የድጋፍ ኮሚቴዎች እንዲሁም ለሕዝብ መብትና ጥቅም መከበር የተመሠረቱ መዋቅሮችን በመጠቀምና የራሱንም አዳዲስ መረቦች በመዘርጋት መንግሥታት፥ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሰብአዊ ጉዳይ ተከታታይ ድርጅቶችና ተቋማት ዘንድ የተጧጧፈ ዘመቻ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ግብረ-ኃይሉ በአስቸኳይ ተሰባስቦ <u>ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ</u> በትላልቅ የዓለም ከተሞች መሪዎች እንዲፈቱ የሚጠይቅ ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በአገር ውስጥም ጫና አሳዳሪ እርምጃዎች ስለመወሰዱበት ሁኔታ ከፖለቲካ ድርጅቶቹ ጋር አስፈላጊውን ምክክር ያደርጋል፡፡

የእስረኞችን ጉዳይ በተሰባሰበ መልክ በሃላፊነት የሚከታተለው ይኸ አካል ብቻ እንዲሆንና ሁሉም ድርጅቶች ሙሉ ትብብር ማድረጋቸው የግብረ-ኃይሉን ሥራ የተሻለ ያቃናል የሚል እምነት አለን፡፡ ለዚህ ተግባራዊነት ሁሉም ወገን ሙሉ ትብብሩን እንዲያሳይና ለፖለቲካና ለኅሊና እስረኞቻችንን ጉዳይ ልዩና አስቸኳይ ትኩረት እንድንሰጥ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡

የኅሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት በጋራ እንቁም!
የተባበረ ትግል ምን ጊዜም አቸናፊ ነው!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)